# የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በጠራው ሀገራዊ ጉባዔ
# የተወሰደ አቋምና የተላለፈ ውሳኔ

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ July 2, 2008 በWashington DC ከተማ በMarriott Washington Hotel የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ከ1፡00-7፡00 P. M. ባካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ፤ በመጀመሪያ ዓመታዊ ሪፖርት በድንበር ኮሚቴው ሊቀመንበር ከቀረበ በኋላ በኮሚቴው የተጋበዙ የክብር እንግዶች በየሙያቸው ንግግር አድርገዋል።
እነዚህም ባለሙያዎች፤

- አንድ የታሪክ ምሑር
- አንድ የሕግ ምሑር
- አንድ የካርቶግራፊ ምሑር
- ሦስት የፖለቲካ ሳይንስ ምሑራን ሲሆኑ፤
- ከድንበሩ አካባቢ ተወላጅ የሆኑ ሁለት ግለሰቦች ደግሞ ተሰጠ ስለሚባለው መሬት ምስክርነት በአካተተ መልኩ መልክዓ ምድራዊ ገለፃ ካደረጉ በኋላ፤ አሁን በድንበሩ አካባቢ አላግባብ እየተፈጸመ ያለውን የእርሻ መተጓጎልና የሕዝብ መንገላታት አስረድተዋል። ከዚያ ቀጥሎ የሃይማኖት አባቶችና የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች ሰፋ ባለ መልኩ ስለድንበሩ ጉዳይ አሳሳቢነት በቁጭት ከተናገሩ በኋላ ጥያቄና መልስ ተስተናግዶ ጉባዔው በሙሉ ድምፅ የሚከተሉትን የአቋም መግለጫና ውሳኔዎች አስተላልፏል።

## (I) አቋም፤

(ሀ) በመለሰ ዜናዊ የጥፋት ቡድን በግንባር ቀደምተኝነት የሚያራምደው አገር ቆርሶ የመስጠት ሴራና በሱዳን መንግሥት በኩል የሚቀርበው የለም መሬት የይገባኛል ክርክር፤

1. ሜጀር (ሻለቃ) ጉዊን የተባለው የእንግሊዝ የጦር መኮንን ያሰመረው ወሰንን ተከትሎ በ1902 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) በአፄ ምኒልክና በእንግሊዝ ንጉሥ የተደረገ ስምምነት አለ ብሎ የሚጠራውን መሠረት በማድረግ፤

2. በ1972-73 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አደረገ የተባለውን ስምምነት (Treaty) መሠረት በማድረግ ነው።

ይሁንና የመጀመሪያውን ማለት የ1902 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) ጉዳይ የክርክር ነጥብ አስመልክቶ የሚከተሉት መረጃዎች ውድቅ ያደርጉታል፤

(i) በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት አሁን ሱዳን ተብሎ ከሚጠራው አገር በጣም ወደ ወስጥ የገባ ስለነበር ኢትዮጵያ አሁን ለሱዳን መሬት መስጠት ሳይሆን የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ ታሪካዊ መሠረት ስለአላት፤

(ii) በ1902 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) አካባቢ (ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላ) እንግሊዝና ጣሊያን በጋራ በመመሳጠር የሰሜንና የምዕራብ ኢትዮጵያን ድንበር ለመግፋት የማይፈጽሙት ሴራ ስለአልነበርና የሜጀር ጉዊን ተልእኮም ከዚያ ተገንጥሎ ስለማይታይ፤

(iii) ሜጀር ጉዊን መሬቱን ሲከልል በግሉ ያደረገው በመሆኑና በኢትዮጵያ በኩል አንድም ተወካይ ስለአልተጨመረ የጉዊን የድንበር ማካለል ተግባር የቪየናን የውል አፈጻጸም ስምምነት(The Vienna Convention on the Law of Treaties) የሚጻረር በመሆኑ፤

(iv) ይህ ጉዊን አካለለ የሚባለው መሬት ምን ጊዜም ከኢትዮጵያ ይዞታ ውጭ ሆኖ ስለማያውቅ፤

(v) ሱዳን እንደ አገር የተፈጠረው በ1956 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) በመሆኑ በ1902 ዓ. ም. የተደረገ ምንም ዓይነት ጉዳይ ሊመለከተው ስለማይችል፤

(vi) የኢትዮጵያ ድንበር ተጠብቆ የኖረው ቅኝ ገዥዎች በዘፈቀደ ባሠመሩት መስመርና ምስክርነት ሳይሆን ኢትዮጵያውያን በደማቸው ዋጋ ከፍለው አስከብረውት የቆየ ስለሆነና ይህ አሁን ወያኔ ለሱዳን ለመስጠት የሚደገስበት ውሃ-ገብ ለም መሬት ደግሞ ለብዙ መቶ ዓመታት በኢትዮጵያ ድንበር ጠባቂዎችና የጎበዝ አለቆች እየተጠበቀ ለአሁኑ ትውልድ የተላለፈ በመሆኑ፤

ሁለተኛውን ማለት የ1972-73 ዓ. ም.(እ.አ.አ.) ጉዳይ የክርክር ነጥብ አስመልክቶ ደግሞ፤ የሚከተሉ መረጃዎች ውድቅ ያደርጉታል፤

በ1972-73 ዓ. ም. የአፄ ኃይለ ሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተስማሙት ነገር ድንበርን መካለል እንደሚያስፈልግ በደፈናው ተስማሙ እንጂ በጊዜው በነበረው ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት፤

(i) የዘውድ ምክር ቤቱ ስላልመከረበትና ስለአላጸደቀው፤

(ii) የሕግ መምሪያው ምክር ቤት (ፓርላማው) ስላልመከረበትና ስለአላጸደቀው፤

(iii) ንጉሠ ነገሥቱ በፊርማቸውና በማኅተማቸው ስለአላጸደቁት፤ እንደ መረጃና ስምምነት (Treaty) ሊቀርብ አይችልም።

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት መረጃዎችና በኢንተራናሽናል የአሠራር ደንብ መሠረት የመለስና የሱዳን መንግሥት መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ ናቸው።

(ለ) የመለሰ ዜናዊ መንግሥት ከአፄ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት መንግሥታት ለሱዳን የሰጡትን መሬት ነው እኛ እያስፈጸምን የምንገኘው ማለቱ ይታወሳል። ይሁንና ከአፄ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት የአገር ሉዓላዊነትን፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የግዛት አንድነት በተመለከተ ሲቻል በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ሳይቻል ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል ድንበሩን ጠብቀውና በአንድ ወቅት በምዕራባውያን ተወስዶ የነበረውን መሬት አስመልሰው ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላለፉ ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን ገጸ-በረከት ለማስረከብ እየተደገሰ ያለውን ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትርና ጥልቀቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሆነውን ውሃ ገብ የኢትዮጵያ ለም መሬት ለሱዳን መስጠት ቅድመ-ወያኔ በሆኑ መንግሥታት የማይታሰብ ጉዳይ ነበር። ይልቁንስ ከወያኔ/ኢሕአዴግ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ይበልጥ የሚታወቁትና ታሪካቸው ሕያው ሆኖ እስካሁን የቆየው የቱርክ፣ የድርቡሽና የሌሎች የኢትዮጵያ ባላንጣዎች በሰሜንና በምዕራብ በኩል ያደረጉትን ጥቃት በራሳቸውና በሕዝባቸው ከፍተኛ መሰዋዕትነት ድንበሩን አስጠብቀው ማቆየታቸው ነው።

በአንፃሩ የመለሰ ዜናዊ ገዢ ቡድን በአለፉት 17 ዓመታት ያደረገው፤ የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ቅልበሳና ሀገሪቱን ቆራርሶ የመስጠት ዘመቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ሲሆን በዓለም ታሪክ ደረጃም በዕብደት ምክንያት የራሱን ከተማ ሮምን እያቃጠለ ይዘፍን ከነበረው ንጉሥ በስተቀር ሌላ አኳያ አይገኝለትም።

የመለስ ዜናዊ የገዢ ቡድን ለኢትዮጵያ ያለው ራዕይ አደገኛና በጥላቻ የተመረዘ ብቻ ሳይሆን ይህን አደጋና ጥላቻ በጀርባው አዝሎ በዓለም መድረክ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ መስሎ መቅረቡ ነው። ባለፉት 17 ዓመታት ኢትዮጵያ ለደረሰባት ጥቃትና ለወደፊትም ሊደርስባት የሚችለው የጎልውና አደጋ ዋና መሠረቱ ይህ የመለስ ዜናዊ ቡድን የለበሰው አሳሳች "የኢትዮጵያ መንግሥት" የሚል ካባና በዚያው ካባ ሥር የሚሠራው አገር የማጥፋት ደባና ተንኮል ነው።

ለዚህ በዋና ምሳሌነት የሚጠቀሰው 1998-99 ዓ. ም. (እ.አ.አ.) በአዲሮብ፣ በጾሮናና በባድሜ ጦርነቶች 70,000 ውድ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ከከፈሉ በኋላ ጉዳዩ አንድም ኢትዮጵያዊ

ጠበቃ ባልተገኘበት ፍርድ ቤት ዳኝነት እንዲሰጥበት ተስማምቶና ራሱም መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ተሚጋች ሆኖ በመቅረብ ቦታዎችን ካስረከበ በኋላ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዞሮ "አሸንፈናል ተሰለፉ" ብሎ በአደባባይ መዋሸቱ ይታወሳል። ይህ በውሸትና በክህደት የተጠመቀ የመለስ ዜናዊ ቡድን አሁን ደግሞ የምዕራብ ድንበራችንን እያስረከበ መሆኑን ከድንበሩ አካባቢ የሚገኙ ተጨባጭ መረጃዎችና በሱዳን መንግሥት ባለሥልጣኖች እየተረጋገጠ ባለበት ወቅት "አልፈረምኩም አልሰጠሁም" የሚል ውሸትና ማደናገሪያ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሰፊው በማሰራጨት ላይ ይገኛል። ይሁንና እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከዚህ ቡድን ሃቅ ወይም ኢትዮጵያዊነት እንደማይጠብቅ የቡድኑ የ17 ዓመት ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊት ገሃድ ምስክር ነው።

## <u>(II) ውሳኔ</u>

(ሀ) የመለሰ ዜናዊ የገዥ ቡድን ራሱ በነደፈው ሕገ መንግሥት በተለይ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 39 በመደጋገፍ የኢትዮጵያን የግዛት ወሰን እንደ ቋሚ ሳይሆን እንደ ጊዜያዊ የሚያዩ በመሆናቸው የዚህ የጥፋት ቡድን ከጥንስሱ እስካሁን ድረስ ዋና ተግባሩ አድርጎ የያዘው ኢትዮጵያን ማፈራረስ በመሆኑ፤ ወደፊትም የሚያደርገው ምሥጢራዊ ሴራ ከዚህ የባሰ እንጂ የተለየ ስለማይሆን፤

(ለ) የመለስ ገዢ ቡድን ኢትዮጵያንና ወላጆቻችንን ለማዋረድ ሲፈልግ አገራችን ምንም ዓይነት ታሪክ የሌላት አድርጎ የሚያቀርብ፤ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ይጠቅመኛል ካለ ደግሞ የአገሪቱን አኩሪ ታሪክ አሽመድምዶና በርዞ የሚያስተጋባ በመሆኑ፤

(ሐ) ይህ ለዜጎቹ ችግር፣ ሥቃይ፣ ሕይወትና ንብረት መጥፋት ደንታ የሌለው የጥፋት ቡድን በጨረቃ የድንበር ምልክት መትከሉና ሱዳኖቹን ማስፈሩ፤ እንዲሁም የሱዳን ወታደር ቋራን ወሮ ንብረት አቃጥሎና ወገኖቻችንን በምርኮ መውሰዱ በትክክል እየታወቀ "የተፈናቀለ አንድም ሰው የለም" ብለው መለሰ ዜናዊና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በአደባባይ በተደጋጋሚ በመዋሸታቸው ቡድኑ በምንም ጉዳይ ቅንጣት ያል የመታመን ባሕሪ እንደሌለው የሚያረጋግጥ በመሆኑ፤

(መ) የመለስ ዜናዊ የጥፋት ቡድን መሬት አሳልፎ ለባዕድ መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ በቤንሻንጉል፣ በምሥራቅና በደቡብ ኢትዮጵያ በሕዝብ ጭፍጨፋና በስርቆት በመሠማራት ከፍተኛ ወንጀል በመፈጸም ላይ ስለሚገኝ፤ ጉባዔው የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፏል፤

1. በአዲሮብ፣ በጾሮናና በባድሜ በኩል ተነስቶ በነበረው ፈታኝ የኢትዮጵያ ጥቅም ማስጠበቂያ ወቅቶች የመለሰ ዜናዊ ቡድን የኢትዮጵያን ድርሻ አሳልፎ ከመስጠት አልፎ ኢትዮጵያን ተሚጋች ሆኖ በመቅረቡ፣ አሁን ደግሞ መለስ ዜናዊ May 20, 2008 ለፓርላማው ባደረገው ንግግር ከኢትዮጵያ ጥቅም አስጠባቂነት ይልቅ የሱዳን ጠበቃ ሆኖ በመቅረቡ በዚህ ቡድን ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም አመኔታ የለውም። ስለዚህ ይህ ቡድን አሁን ከሱዳን መንግሥት ጋር የሚያደርገው ምንም ዓይነት የድንበር ውል በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት አይኖረውም፤

2. የመለሰ ዜናዊ ቡድን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማጥፋት በመላው ኢትዮጵያ የሚያደርገው ሕዝብን ማጋጨትና ሕዝብን የማጥፋት ዘመቻ ለአገራችን በጣም አደገኛ መሆኑን በመገንዘብ ጉባዔው በሙሉ ድምፅ የሚከተሉትን አገራዊ ጥሪዎች ያቀርባል፤

(i) የተቃዋሚ ድርጅቶችም የአገራቸው ኀልውና ደብዛው ከመጥፋቱ በፊት ለአንዲት እናት አገር ሲሉ ያላቸውን ልዩነት አቻችለው ኢትዮጵያን ለማዳን በአንድነት ለመቆም ቆራጥ እርምጃ እንዲወስዱ፤

(ii) የኢትዮጵያ ሲቪክ ማኅበራት የአላቸውን አቅም ተጠቅመው ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው ዘመቻ በትጋት እንዲሳተፉ፤

(iii) የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ የአገሩን ዳር ድንበር ማስደፈር የሚያሳፍር መሆኑን ተረድቶ ኢትዮጵያን ለማዳን በሚደረገው ዘመቻ ታሪካዊ ግዴታውን እንዲወጣ፤

(iv) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አገርን ለማዳን በሚደረገው ዘመቻ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን፤

(v) ለመኖር ብቻ ብለው በወያኔ/ኢሕአዴግ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው በማገልገል ላይ ያሉ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች አገር ከሌለ የእነሱም እጣና ፈንታ አብሮ የሚጠፋ መሆኑንና የታሪክ ተጠያቂና ተወቃሽ መሆናቸውን አውቀው በወያኔ/ኢሕአዴግ የጥፋት ዘመቻ ያላቸውን ትብብር እንዲያቆሙና ለወገኖቻቸውና ለልጆቻቸው ሲሉ ከኢትዮጵያ ጎን እንዲቆሙ፤

(vi) በአገር ወስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቀን የተወሰኑ ሰዓቶች በመሰዋት ባለመሰልቸትና ባለማቋረጥ የመለሰ ዜናዊ የጥፋት ቡድን በኢትዮጵያ ላይ እየፈጸመ ያለውን መሬት አሳልፎ የመስጠት ወንጀል ለሃይማኖት አባቶች፣ ለአርሶ አደሩ፣ ለሠራተኛው፣ ለወጣቱ፣ ለአረጋውያን፣ ለፓርላማ አባላትና ለወታደሩ በሚቻለው ዘዴ ሁሉ እንዲያስተላልፍ፤

(vii) የመለሰ ዜናዊ የጥፋት ቡድን የሚያደርገው የአገር ክህደት(Treason)፣ የሕዝብ መጨረስ (Genocide)፣ የአገር ንብረት ምዝበራና ዘረፋ (Pillage of a nation) ወንጀሎች ከፍተኛ በመሆናቸው፤ በሰፊው የሚመዘግብና የሚያጠናክር አንድ ኮሚቴ በኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አማካይነት እንዲቋቋምና የተቋቋመው ኮሚቴ በዓለም አቀፍ የፍትሕ መድረኮች አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ፤

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በልጆቿ ይጠበቃል!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!

እኛ በዋሽንግተን ከተማ በማሪዮት ዋሽንግተን ሆቴል አዳራሽ የተገኘን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን፤

ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ. ም. (July 02, 2008)
e-mail:- ethiosudanborder@yahoo.com